**ለተቀባዮችና ተንከባካቢዎች የቀረበ የመረጃ ቅጽ**

**የኮሮና ቫይረስ 2019 (COVID-19) በሽታን ለመከላከል**
**የሚረዳ የኖቫቫክስ (NOVAVAX) ኮቪድ-19 ክትባት**

**በከባድ የመተንፈሻ ሲንድረም ኮሮናቫይረስ 2 (SARS-CoV-2) ምክንያት የሚመጣውን የኮሮና ቫይረስ በሽታን 2019 (ኮቪድ-19) ለመከላከል የሚረዳው የኖቫቫክስ (NOVAVAX) ኮቪድ-19 ክትባት እየተሰጠዎት ነው።**

**አጋዥ የሆነው የኖቫቫክስ (NOVAVAX) የCOVID-19 ክትባት የሚከተሉትን ለመስጠት ከዩኤስ የምግብ እና የመድኃኒት አስተዳደር (FDA) "የአስቸኳይ ጊዜ የመጠቀም ፍቃድ (EUA) አግኝቷል፥**

- ዕድሜያቸው 12 ዓመት እና ዚያ በላይ ለሆኑ ሰዎች በሁለት ዶዝ የመጀመሪያ ተከታታይ ክትባት
- ፍቃድ ካለው ወይም ከተፈቀደለት የCOVID-19 ክትባት የመጀመሪያ ተከታታይ ክትባት ለወሰዱና ክትባቱን ከተከተቡ ቢያንስ 6 ወር ለሆናቸው የሚከተሉት ግለሰቦች የመጀመሪያ አጋዥ ዶዝ፥
  - ዕድሜያቸው 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሌሎች በ FDA ፍቃድ ያገኘ mRNA ባይቫለንት/ Bivalent[1] የኮቪድ-19 አጋዥ ክትባት ማግኘት ላልቻሉ ወይም በህክምና ለማይፈቀድላቸው ግለሰቦች፣
  - ዕድሜያቸው 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ እና አጋዥ የሆነውን የናቫቫክስ (Novavax) የኮቪድ-19 ክትባት ለመከተብ ለሚመርጡ እና የናቫቫክስ ክትባት ካልሆነ በቀርን የኮቪድ-19 አጋዥ ክትባት ለማይከተቡ ግለሰቦች።

ይህ የመረጃ ቅጽ በአሁኑ ወቅት የCOVID-19 ወረርሽኝ በመከሰቱ ምክንያት ሊወስዱት ስለሚችሉት አጋዥ ስለሆነው የኖቫቫክስ (NOVAVAX) የCOVID-19 ክትባት ስጋቶችና ጥቅሞችን ለመረዳት የሚረዳዎ መረጃ ይዟል። ጥያቄዎች ካሉዎ የክትባት አቅራቢዎን ያነጋግሩ።

አጋዥ የሆነው የኖቫቫክስ (NOVAVAX) የCOVID-19 ክትባት ሁሉንም ሰው ላይከላከል ይችላል።

ይህ የመረጃ ቅጽ ማሻሻያ ሊደረግበት ይችላል። በጣም የቅርብ የመረጃ ቅጽ ለማግኘት እባክዎ http://www.NovavaxCovidVaccine.com የሚለውን ሊንክ ይመልከቱ።

**ይህንን ክትባት ከማግኘትዎ በፊት ማወቅ ያለብዎት ኮቪድ-19 ምንድነው?**

የCOVID-19 በሽታ SARS-CoV-2 ተብሎ በሚጠራ የኮሮና ቫይረስ ምክንያት የሚመጣ በሽታ ነው። ይህ አይነቱ የኮሮና ቫይረስ ከዚህ በፊት ታይቶ አያውቅም። በቫይረሱ ከተያዘ ከሌላ ሰው ጋር ንክኪ በማድረግዎ ምክንያት በCOVID-19 ሊያዙ ይችላሉ። በሽታው በዋናነት ሌሎች የሰውነት ክፍሎችን ሊያጠቃ የሚችል የመተንፈሻ አካል ህመም ነው። በCOVID-19 የተያዙ ሰዎች ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ ህመም የሚደርሱ የተለያዩ ምልክቶች እንደታዩባቸው ሪፖርት ተደርጓል። ምልክቶቹ ለቫይረሱ ከመጋለጥ በኋላ ከ2 እስከ 14 ቀናት ውስጥ ሊታዩ ይችላሉ። ምልክቶቹ ትኩሳት ወይም ብርድ ብርድ ማለትን፣ ሳልን፣ የትንፋሽ ማጠርን፣ ድካምን፣ የጡንቻ ወይም የሰውነት ህመምን፣ አዲስ የሚፈጠር የጣዕም ወይም ሽታ አለመለየትን፣ የጉሮሮ መሰርሰርን፣ የአፍንጫ ፈሳሽ መብዛትን፣ ማቅለሽለሽ ወይም ማስመለስን፣ ተቅማጥን ሊይዙ ይችላሉ።

---

[1] ፍቃድ የተሰጣቸው ባይቫለንት/ Bivalent የCOVID-19 ክትባትቶች የመጀመሪያውን SARS-CoV-2ን እና ኦሚክሮን/Omicron BA.4/BA.5 SARS-CoV-2 ስፓይክ ፕሮቲንን ያመነጫሉ።

## **አጋዥ የሆነው የኖቫቫክስ (NOVAVAX) የኮቪድ-19 ክትባት ምንድነው?**

አጋዥ የሆነው የኖቫቫክስ (NOVAVAX) የCOVID-19 ክትባት ፍቃድ ያልተሰጠው COVID-19ን ሊከላከል የሚችል ክትባት ነው። አጋዥ የሆነው የኖቫቫክስ (Novavax) የCOVID-19 ክትባት የመጀመሪያውን የSARS-CoV-2 ስፓርክ ፕሮቲንን የያዘ ሞኖቫለንት ክትባት ነው።

FDA በአስቸኳይ ጊዜ የመጠቀም ፍቃድ (EUA) ስር እድሜያቸው 12 አመትና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሰዎች COVID-19ን ለመከላከል ለመጀመሪያ ተከታታይ ክትባት እና እድሜያቸው 18 አመትና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሰዎች ለመጀመሪያ አጋዥ ዶዝ ለአስቸኳይ ጊዜ አጋዥ የሆነውን የኖቫቫክስ (NOVAVAX) የCOVID-19 ክትባትን መጠቀምን ፈቅዷል። እድሜያቸው 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ግለሰቦች የሚሰጠው አጋዥ ዶዝ ፈቃድ የሚተገበረው በ FDA ፍቃድ ያገኙ ወይም የተፈቀደላቸው mRNA ባይቫለንት/ Bivalent የኮቪድ-19 አጋዥ ክትባቶች ማግኘት ላልቻሉ ወይም በህክምና ለማይፈቀድላቸው፣ እና አጋዥ የሆነውን የናቫቫክስ (Novavax) የኮቪድ-19 ክትባት ለመከተብ ለሚመርጡ እና የናቫቫክስ ክትባት ካልሆነ በቀርን የኮቪድ-19 አጋዥ ክትባት ለማይከተቡ ግለሰቦች ነው።

ስለ EUA ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት በዚህ የመረጃ ቅጽ መጨረሻ ላይ "**የአስቸኳይ ጊዜ የመጠቀም ፍቃድ (EUA) ምንድን ነው?**" የሚለውን ክፍል ይመልከቱ።

## **አጋዥ የሆነውን የኖቫቫክስ (NOVAVAX) የCOVID-19 ክትባትን ከመውሰድዎ በፊት ለክትባት አቅራቢዎ መግለጽ ያለብዎ ምንድን ነው?**

ለክትባት አቅራቢዎ የሚከተሉትን ጨምሮ ስለ ሁሉም የጤና ሁኔታዎችዎ ይንገሩት:

- የትኛውም አላርጂዎች ካሉብዎ
- ማዮካርዲቲስ (የልብ ጡንቻ መቆጣት) ወይም ፔሪካርዲቲስ (የልብ ውጫዊ አገናኝ መስመሮች መቆጣት) ያለብዎ ስለመሆኑ
- ትኩሳት ካለብዎ
- የደም መፍሰስ ችግር ወይም የደም መቅጠን ካለብዎ
- የበሽታ መከላከል አቅምዎ የተዳከመ ከሆነ ወይም የበሽታ መከላከል ስርአትዎ ላይ ተጽእኖ የሚፈጥር መድሀኒት እየወሰዱ ከሆኑ
- ነፍሰ ጡር ከሆኑ ወይም የማርገዝ እቅድ ካሉዎ
- የሚያጠቡ ከሆነ
- ሌላ የCOVID-19 ክትባት ከወሰዱ
- ከክትባት ጋር በተያያዘ እራስዎን ስተው የነበር ከሆነ

## **አጋዥ የሆነውን የኖቫቫክስ (NOVAVAX) ኮቪድ-19 ክትባት ማን ማግኘት የለበትም?**

የሚከተሉት ካሉብዎ አጋዥ የሆነውን የኖቫቫክስ (NOVAVAX) የCOVID-19 ክትባትን

መውሰድ የለብዎትም: ቀደም ሲል የክትባቱን የመጀመሪያውን ዶዝ ከወሰዱ በኋላ ከባድ አለርጂ

ካጋጠሙዎ
በክትባቱ በየትኛውም ግብአት ምክንያት ከባድ አለርጂ ካጋጠሙዎ

## **አጋዥ የሆነው የኖቫቫክስ (NOVAVAX) የCOVID-19 ክትባት ግብአቶች ምንድን ናቸው?**

ኖቫቫክስ የCOVID-19 ክትባት/Novavax COVID-19 Vaccine የሆነው አድጁቫንትድ/Adjuvanted ከተበከሉ የSf9 (fall armyworm) የነፍሳት ሴሎች ከሚዘጋጁት ባኩሎቫሪስ እና ከሳሙና ዛፍ (Quillajasaponaria Molina) የሚገኙትን ሳፖኒንስን ከሚይዘው Matrix- M$^{TM}$ አጁቫንት የሚገኘውን የSARS-CoV-2 ስፓርክ ፕሮቲን ድጋሚ ውህድን ይይዛል።

ሌሎች ግብዓቶች ኮሌስትሮልን፣ ፎስፌቲዲልኮሊንን፣ ፖታሺየም ዳይሀይድሮጂን ፎስፌትን፣ ፖታሺየም ክሎራይድን፣ ዳይሶዲየም ሀይድሮጂን ፎስፌት ዳይሀይድሬትን፣ ሶዲየም ክሎራይድን፣ ዳይሶዲየም ሀይድሮጅን ፎስፌት ሄፕታይሀይድሬትን፣ ሶዲየም ዳይሀይድሮጅን ፎስፌት ሞኖሀይድሬትን፣ ፖሊሶርቤት 80ን እና የመውጊያ ውሀን ያጠቃልላሉ። ከዚህም ሌላ፣ ክትባቱ አነስተኛ መጠን ያለው ባኩሎቫይረስ እና የነፍሳት ህዋስ ፕሮቲኖችን እና DNA ሊይዝ ይችላል።

### አጋዥ የሆነው የኖቫቫክስ (NOVAVAX) የኮቪድ-19 ክትባት የሚሰጠው እንዴት ነው?

አጋዥ የሆነው የኖቫቫክስ (NOVAVAX) የCOVID-19 ክትባት በመርፌ መልኩ በጡንቻዎ ላይ ይሰጥዎታል።

<u>የመጀመሪያ ተከታታይ ክትባት</u>፥ አጋዥ የሆነው የኖቫቫክስ (NOVAVAX) የCOVID-19 ክትባት በ3 ሳምንት ልዩነት በ2 ተከታታይ ዶዝ ይሰጣል።

<u>አጋዥ ዶዝ</u>፥ አጋዥ የሆነው የኖቫቫክስ (NOVAVAX) የCOVID-19 ክትባት ፍቃድ ካለው ወይም ከተፈቀደለት የCOVID-19 ክትባት የመጀመሪያ ተከታታይ ክትባት ካጠናቀቁ በኋላ ቢያንስ 6 ወር ለሆናቸው ግለሰቦች እንደ መጀመሪያ አጋዥ ዶዝ ሊሰጥ ይችላል።

### አጋዥ የሆነው የኖቫቫክስ (NOVAVAX) የCOVID-19 ክትባት ከዚህ ቀደም ሲል ጥቅም ላይ ውሏል?

አጋዥ የሆነው የኖቫቫክስ (NOVAVAX) የCOVID-19 ክትባት ፍቃድ ያላገኘ ክትባት ነው። በህክምና ሙከራዎች ወደ 28,000 የሚጠጉ እድሜያቸው 12 አመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች አጋዥ የሆነው የኖቫቫክስ (NOVAVAX) የCOVID-19 ክትባትን ቢያንስ አንድ ዶዝ ወስደዋል።

### አጋዥ የሆነው የኖቫቫክስ (NOVAVAX) የCOVID-19 ክትባት የሚያስገኛቸው ጥቅሞች ምንድን ናቸው?

አጋዥ የሆነው የኖቫቫክስ (NOVAVAX) ኮቪድ-19 ክትባት ኮቪድ -19ን በመከላከል ታይቷል። የክትባቱ ከCOVID-19 መከላከል የቆይታ ጊዜ በአሁኑ ወቅት አልታወቀም።

### አጋዥ የሆነው የኖቫቫክስ (NOVAVAX) የCOVID-19 ክትባት የሚያስከትላቸው ስጋቶች ምንድን ናቸው?

አጋዥ የሆነው የኖቫቫክስ (NOVAVAX) የCOVID-19 ክትባት ከባድ አለርጂ የሚያስከትልበት አጋጣሚ በጣም ጥቂት ነው። ከባድ አለርጂ በዋናነት የሚያጋጥመው አጋዥ የሆነው የኖቫቫክስ (NOVAVAX) ኮቪድ-19 ክትባት ከተወሰደ በኋላ ካሉት ጥቂት ዲቃዎች ጀምሮ እስከ አንድ ሰአት ያክል ባለው ጊዜ ውስጥ ነው። በዚህም ምክንያት የክትባት አቅራቢዎ የክትባቱን ሁኔታ ለመቆጣጠር እንዲያስችለው ክትባቱን በወሰዱበት ቦታ እንዲቆዩ ሊጠይቅዎት ይችላል። የከባድ አለርጂ ምልክቶች የሚከተሉትን ሊያጠቃልሉ ይችላሉ፡

- የመተንፈስ ችግር
- የፊት ወይም ጉሮሮ እብጠት
- የልብ ምት መፍጠን
- ከባድ የሙሉ ሰውነት መንደብደብ
- መደበትና ድካም

ማዮካርዲቲስ (የልብ ጡንቻ መቆጣት) ወይም ፔሪካርዲቲስ (የልብ ውጫዊ አገናኝ መስመሮች መቆጣት) በጥቂት ክትባቱን በወሰዱ ሰዎች ላይ ተከስቷል። በእነዚህ አብዛኞቹ ሰዎች ላይ ምልክቶቹ መታየት የጀመሩት ክትባቱን በወሰዱ በ 10 ቀናት ውስጥ ነው። ይህ የሚያጋጥምበት እድል በጣም ዝቅተኛ ነው። ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ የትኛውም የሚከተሉት ምልክቶች ከታዩብዎ ወዲያውኑ የህክምና ክትትል ያድርጉ፡

- የደረት ህመም

- ትንፋሽ ማጠር
- የፈጣን አተነፋፈስ፣ የልብ መርገብገብ ወይም መውጋት ስሜት

አጋዥ በሆነው የኖቫቫክስ (NOVAVAX) የCOVID-19 ክትባት የህክምና ሙከራዎች ሪፖርት የተደረጉት የጎኒዮሽ ውጤቶች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፥

- ማዮካርዲቲስ (የልብ ጡንቻ መቆጣት)
- ፔሪካርዲቲስ (የልብ ውጫዊ አገናኝ መስመሮች መቆጣት)
- መርፌ የተወጋበት በታዎች ላይ የሚታዩ: ህመም/የብሽሽት ክፍል መቆጣት፣ የቆዳ መቅላት እና ማሳከክ።
- ጠቅላላ አሉታዊ ምላሾች: ድካም ወይም በጥቅሉ ደህና ያለመሆን ስሜት፣ የጡንቻ ህመም፣ ራስ ምታት፣ የመገጣጠሚያ ህመም፣ ማቅለሽለሽ፣ ማስመለስ፣ ትኩሳት፣ ብርድ ብርድ ማለት
- እንደ ሽፍታ እና የፊት እብጠት ያሉ አለርጂዎች
- የብሽሽት እብጠት

አጋዥ የሆነው የኖቫቫክስ (NOVAVAX) ኮቪድ-19 ክትባት ከተፈቀዱ በኋላ ጥቅም ላይ ሲውል ሪፖርት የተደረጉ የጎንዮሽ ጉዳቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፥

- ከባድ አለርጂ
- ማዮካርዲቲስ (የልብ ጡንቻ መቆጣት)
- ፔሪካርዲቲስ (የልብ ውጫዊ አገናኝ መስመሮች መቆጣት)
- ፓራቲሲያ (በቆዳ ውስጥ ያልተለመደ ስሜት እንደ መንቀጥቀጥ ወይም የመሳብ ስሜት)፣ ሀይፖቲሲያ (ስሜት መቀነስ ወይም ስሜታዊነት፣ በተለይም በቆዳ ውስጥ)

እነዚህ አጋዥ የሆነው የኖቫቫክስ (NOVAVAX) የኮቪድ-19 ክትባት ሊሆኑ የሚችሉ የጎንዮሽ ጉዳቶች ላይሆኑ ይችላሉ። ከባድና ያልተጠበቁ የጎኒዮሽ ውጤቶች ሊያጋጥሙ ይችላሉ። አጋዥ የሆነው የኖቫቫክስ (NOVAVAX) የCOVID-19 ክትባት አሁንም በህክምና ሙከራዎች ጥናት እየተደረገበት ነው።

**የጎኒዮሽ ውጤቶች ካጋጠሙኝ ምን ማድረግ አለብኝ?**

ከባድ አለርጂ ካጋጠመዎት ወደ 9-1-1 ይደውሉ ወይም በአቅራቢያዎ ወደሚገኝ ሆስፒታል ይሂዱ።

የሚረብሹዎት ወይም የማይሄዱ የጎንዮሽ ጉዳቶች ካሉዎት ለክትባት አቅራቢው ወይም ለጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ይደውሉ።

የክትባቱን የጎኒዮሽ ውጤቶች ለFDA እና ለበሽታ መቆጣጠሪያ እና መከላከያ ማእከል (CDC) **የክትባት አሉታዊ ክስተት ሪፖርት ማቅረቢያ ሲስተም (VAERS)** ሪፖርት ያድርጉ። የVAERS የነጻ ጥሪ መስመር 1-800-822-7967 ነው ወይም በኦንላይን በ https://vaers.hhs.gov/reportevent.html ሪፖርት ያድርጉ። እባክዎ በሪፖርት ማቅረቢያ ቅጹ በሳጥን #18 ስር በሚገኘው የመጀመሪያው መስመር ላይ "አጋዥ የሆነው የኖቫቫክስ (NOVAVAX) የCOVID-19 ክትባት EUA" የሚለውን ያካቱ።

ከዚህ በተጨማሪም የጎኒዮሽ ውጤቶቸን ለኖቫቫክስ (NOVAVAX) Inc. ከዚህ በታች በተገለጸው የግንኙነት መረጃ ሪፖርት ሊያደርጉ ይችላሉ።

| ድረ ገጽ | የፋክስ ቁጥር | ስልክ ቁጥር |
|---|---|---|
| www.NovavaxMedInfo.com | 1-888-988-8809 | 1-844-NOVAVAX<br>(1-844-668-2829) |

እንዲሁም በ **V-safe** ለመመዝገብ አማራጭ ሊሰጥዎት ይችላል። **V-safe** የCOVID-19 ክትባትን ከወሰዱ ሰዎች ስላጋጠሟቸው የጎኒዮሽ ውጤቶች ለማረጋገጥ የጽሁፍ መልእክትና የድረገጽ ጥናቶችን የሚጠቀም የፍቃደኝነት ስማርት ስልክን መሰረት ያደረገ መሳሪያ ነው። **V-safe** ለCDC ስለ COVID-19 ክትባቶች አስተማማኝነት ለመቆጣጠር የሚረዱትን ጥያቄዎች ይጠይቅዎታል። **V-safe** በተጨማሪም አስፈላጊ ከሆነ የሁለተኛውን ዶዝ ማስታወሻ ይሰጣል እንዲሁም ተሳታፊዎች የCOVID-19 ክትባትን መውሰዳቸውን ተከትሎ ከባድ የጤና ተጽእኖ እንደተፈጠረባቸው ሪፖርት የሚያደርጉ ከሆነ የቀጥተኛ የCDC የስልክ ክትትል ያደርጋል። እንዴት እንደሚመዘገቡ በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት: www.cdc.gov/vsafeን ይጎብኙ።

**አጋዥ የሆነው የኖቫቫክስ (NOVAVAX) የCOVID-19 ክትባትን ላለመውሰድ ብወስን ምን ይሆናል?**

በ EUA ስር፣ አጋዥ የሆነው የኖቫቫክስ (NOVAVAX) መውሰድ ወይም አለመውሰድ የእርስዎ ምርጫ ነው። ክትባቱን ላለመውሰድ ቢወስኑ የህክምና እንክብካቤ ደረጃዎ ላይ ለውጥ አይፈጥርም።

**COVID-19ን ለመከላከል በአጋዥ የሆነው የኖቫቫክስ (NOVAVAX) የCOVID-19 ክትባት ምትክ የሚቀርቡ ሌሎች አማራጮች አሉ?**

ለመጀመሪያው ክትባት፣ ኮቪድ-19ን ለሚከላከል የሚቀርቡ ሌሎች አማራጮች በFDA-የተፈቀዱትን እድሜያቸው 12 ዓመት እና ከዛ በላይ ለሆኑ የ COMIRNATY (COVID-19 Vaccine, mRNA) እና እድሚያቸው 18 ዓመት እና ከዛ በላይ ለሆኑSPIKEVAX (COVID-19 Vaccine, mRNA) የCOVID-19 ክትባት ናቸው። የSARS-CoV-2 ኦሚክሮን/ Omicron ንጥረ ነገርን የሚይዙ የባይቫለንት/ Bivalent ክትባቶችን ጨምሮ ሌሎች COVID-19ን የሚከላከሉ ክትባቶች ሊቀርቡ ይችላሉ።

**ሌሎች ክትባቶች እየወሰድኩ ባለበት በተመሳሳይ ጊዜ አጋዥ የሆነውን የኖቫቫክስ (NOVAVAX) የኮቪድ-19 ክትባትን መቀበል እችላለሁን?**

አጋዥ የሆነው የኖቫቫክስ (NOVAVAX) የኮቪድ-19 ክትባት ከሌሎች ክትባቶች ጋር በተመሳሳይ ጊዜ ስለመስጠት ለFDA መረጃ አልቀረበም። አጋዥ የሆነውን የኖቫቫክስ (NOVAVAX) የኮቪድ-19 ክትባት ከሌሎች ክትባቶች ጋር ለመውሰድ እያሰቡ ከሆነ፣ ስለ አማራጮችዎ ከጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ጋር ይወያዩ።

**ነፍሰ ጡር ወይም የማጠባ ቢሆን ምን ይሆናል?**

ነፍሰ ጡር ከሆኑ ወይም የሚያጠቡ ከሆነ ስለ አማራጮችዎ ከጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ጋር ይወያዩ።

በእርግዝና ወቅት አጋዥ ለሆነው የኖቫቫክስ (NOVAVAX) የCOVID-19 ክትባት በተጋለጡ ሴቶች ላይ የእርግዝና ውጤቶችን የሚከታተል የእርግዝና ተጋላጭነት ቁጥጥር አለ። በእርግዝና ወቅት አጋዥ የሆነውን የኖቫቫክስ (NOVAVAX) የCOVID-19 ክትባት የተከተቡ ሴቶች በዚህ የቁጥጥር መዝገብ ላይ ወደ https://c-viper.pregistry.com/ በመሄድ እንዲመዘገቡ ይበረታታሉ።

**አጋዥ የሆነው የኖቫቫክስ (NOVAVAX) የCOVID-19 ክትባት በCOVID-19 እንድያዝ ያደርገኛል?**

አይ። አጋዥ የሆነው የኖቫቫክስ (NOVAVAX) የኮቪድ-19 ክትባት SARS-CoV-2 ን አልያዘም እና ኮቪድ-19 ሊያሲዞ አይችልም።

**የክትባት ካርድዎን ይያዙ**

የመጀመሪያውን ዶዝ ከወሰዱ በኋላ ሁለተኛውን አጋዥ የሆነው የኖቫቫክስ (NOVAVAX) የCOVID-19 ክትባት ለመውሰድ በሚመለሱበት ወቅት የሚያሳዩት የክትባት ካርድ ይሰጥዎታል። ተመልሰው በሚመጡበት ወቅት ካርዱን መያዝዎን አይርሱ።

**ተጨማሪ መረጃ**

ጥያቄዎች ካሉዎ ከዚህ በታች የተገለጸውን ድረገጽ ይጎብኙ ወይም ከታች በተገለጸው ስልክ ቁጥር ይደውሉ።

በጣም የቅርብ የመረጃ ቅጾችን ለማግኘት እባክዎ ከዚህ በታች የቀረበውን የQR ኮድ ስካን ያድርጉ።

| **አጋዥ የሆነው የኖቫቫክስ (NOVAVAX) Covid-19 ድረገጽ** | **ስልክ ቁጥር** |
|---|---|
| www.NovavaxCovidVaccine.com | 1-844-NOVAVAX<br>(1-844-668-2829) |

**ተጨማሪ መረጃ እንዴት አገኛለሁ?**

- የክትባት አቅራቢውን ይጠይቁ።
- CDCን በ https://www.cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/index.html ይጎብኙ።
- FDAን በ https://www.fda.gov/emergency-preparedness-and-response/mcm-legal-regulatory-and-policy-framework/emergency-use-authorization ይጎብኙ።
- የግዛትዎን የአካባቢዎን ወይም የማህበረሰብ ጤና መምሪያ ያነጋግሩ።

**የክትባት መረጃዬ የት ይመዘገባል?**

ክትባት አቅራቢው የክትባት መረጃዎን በግዛት/አካባቢ የክትባት መረጃ ሲስተም (IIS) ወይም ሌላ የተመደበ ሲስተም ላይ ሊያካትት ይችላል። ይህ ሁለተኛውን ዶዝ ለመውሰድ በሚመለሱበት ወቅት ተመሳሳዩን ክትባት እንደሚወስዱ ለማረጋገጥ ያስችላል። ስለ IISዎች የተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት: https://www.cdc.gov/vaccines/programs/iis/about.htmlን ይጎብኙ።

**የCOVID-19 ክትባትን ለማግኘት የመከተቢያ ክፍያ እከፍላለሁ?**

አይ። በአሁኑ ወቅት ክትባት አቅራቢው የክትባቱን ዶዝ ለመስጠት ሊያስከፍልዎ የማይችል ከመሆኑም በተጨማሪ የሚወስዱት የCOVID-19 ክትባትን ብቻ ከሆነ ለክትባቱ መውሰጃ ክፍያ ወይም የትኛውም ሌላ ክፍያ ከኪስዎ አይከፍሉም። ሆኖም የክትባት አቅራቢዎች ለክትባቱ ወሳጆች የCOVID-19 ክትባት መስጫ ክፍያዎች ሽፋን ከሚሰጥ ፕሮግራም ወይም እቅድ (የግል የመድን ዋስትና፣ Medicare፣ Medicaid፣ የመድን ዋስትና ላልተገባላቸው ተቀባዮች HRSA COVID-19 Uninsured Program ፕሮግራም) ተገቢውን መልሶ ክፍያ ሊጠይቁ ይችላሉ።

**የሚጠረጠሩ የማጭበርበር ጉዳዮችን የት ሪፖርት ማድረግ እችላለሁ?**

የCDC የCOVID-19 ክትባት ፕሮግራም መስፈርቶች ላይ ስለሚፈጸሙ ስለ የትኛውም ጥሰቶች የሚያውቁ ግለሰቦች እነዚህን ለዩኤስ የጤናና ሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ፣ የዋና መርማሪ ጽ/ቤት በ1-800-HHS-TIPS ወይም TIPS.HHS.GOV ሪፖርት እንዲያደርጉ ይበረታታሉ።

**የጉዳት የአጸፋ እርምጃዎች የካሳ ፕሮግራም ምንድን ነው?**

የጉዳት የአጸፋ እርምጃዎች የካሳ ፕሮግራም (CICP) ይህን ክትባት ጨምሮ በተወሰኑ መድሀኒቶች ወይም ክትባቶች የተነሳ ከባድ ጉዳት የሚደርስባቸው ሰዎች የሚከፍሏቸው የህክምና እንክብካቤ ወጪዎች እና ሌሎች ልዩ ወጪዎች እንዲከፈሏቸው የሚያግዝ የፌደራል ፕሮግራም ነው። በጠቅላላው የካሳ ጥያቄው ክትባቱ ከተወሰደበት ቀን ጀምሮ በአንድ (1) አመት ውስጥ ለCICP መቅረብ አለበት። ስለዚህ ፕሮግራም የተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት www.hrsa.gov/cicp/ ን ይጎብኙ ወይም በስልክ ቁጥር 1-855-266-2427 ይደውሉ።

**የአስቸኳይ ጊዜ የመጠቀም ፍቃድ (EUA) ምንድን ነው?**

የአስቸኳይ ጊዜ የመጠቀም ፍቃድ (EUA) እንደ የወቅቱ የCOVID-19 ወረርሽኝ የመሳሰሉ የማህበረሰብ ጤና አስቸኳይ ሁኔታዎች በሚያጋጥሙበት ወቅ ክትባቶችን ጨምሮየህክምና ምርቶች እንዲቀርቡና ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚያመቻች አሰራር ነው። EUA በCOVID-19 ወረርሽኝ ቆይታ ውስጥ ለአስቸኳይ ጊዜ መድሀኒቶችን እና የባዮሎጂካል ምርቶችን ለመጠቀም አሳማኝ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ይህን በሚፈቅደው የጤናና ሰብአዊ አገልግሎቶች ጽ/ቤት (HHS) መግለጫ ድጋፍ አግኝቷል። በአስቸኳይ ጊዜ የአጠቃቀም ፍቃድ የተሰጠው ምርት ከ FDA ፍቃድ ካገኘ ምርት ጋር በ FDA አንድ አይነት የግምገማ ሂደት አይደረግለትም።

FDA የተወሰኑ መስፈርቶች ሲሟሉ EUA ሊሰጥ የሚችል ሲሆን መስፈርቶቹ በቂ፣ የተፈቀዱ፣ ዝግጁ አማራጮች አለመገኘትን ይይዛሉ። በተጨማሪም የFDA ውሳኔ በሚቀርቡለት ምርቱ በCOVID-19 ወረርሽኝ መከሰት ወቅት COVID-19ን ለመከላከል ውጤታማ ሊሆን እንደሚችል እና የምርቱ የታወቁና ሊሰሩ የሚችሉ ጥቅሞችን እና ከምርቱ የታወቁና ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶች ይልቅ ጥቅሞቹ እንደሚያመዝኑ በሚያሳዩ ሳይንሳዊ ማስረጃዎች ላይ ሙሉ በሙሉ ይመሰረታል። በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ወቅት ምርቱ ጥቅም ላይ እንዲውል እነዚህ ሁሉ መመዘኛዎች መሟላት አለባቸው።

ካልተቋረጠ ወይም ካልተሻረ በስተቀር (ይህ ከሆነ ግን፣ ከዚያን ጊዜ በኋላ ምርቱ ጥቅም ላይ ሊውል አይችልም)፣ የ ኮቪድ-19 የ EUA አስቸኳይ ጊዜ የአጠቃቀም ፍቃድ አስፈላጊነት እስካለ ድረስ፣ የዚህን ምርት EUA ተግባራዊ እንደሆነ የሚቆይ ይሆናል።

የተመረተው ለ፥
Novavax, Inc., Gaithersburg, MD,

20878 C20101US-001

የተሻሻለበት ቀን፥ ጥቅምት/19/2022
©2022 Novavax, Inc. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።

ይህ የመረጃ ቅጽ ለኤሌክትሮኒክ የሕክምና መረጃዎች/የክትባት የመረጃ ሲስተሞች ለክትባት ተቀባዩ የቀረበ መሆኑን ለማረጋገጥ ስካን ያድርጉ።

GDTI: 0886983000370